ዜና
አመዝሄ



## በዚህ ዕትም ውስጥ

ለጎርፍ አደጋ ተጎጂ ወገኖች ከ10 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ፣ ከ86 ሺህ በላይ የቁሳቁስ ፣ ከ14 ሺህ በላይ የአልባሳት እና 652 የመጠለያ ዕርዳታዎች ተከፋፍለዋል
*ገጽ 3*

በጐርፍ አደጋ ለተጐዱ ወገኖች መርጃ ከ ብር 23 ሚሊዮን በላይ ተለግሷል
*ገጽ 4*

በጐርፍ ለተጐዱ ወገኖች መርጃ ከ 1 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ በውጭ መንግስታትና ድርጅቶች ተለግሷል
*ገጽ 5*

**መልካም አዲስ ዓመት**

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 5529259
ፖ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣www.dppc.gov.et



# ለጎርፍ አደጋ ተጎጂ ወገኖች መርጃ ከ27 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ዕርዳታ ያስፈልጋል

በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በተከሰተው የጎርፍ አደጋ ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉና ተጎጂ ለሆኑ 199 ሺህ ወገኖች መርጃ በጠቅላላው 27 ሚሊዮን 099 ሺህ 526 የአሜሪካን ዶላር ለአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ እና ለሌሎች ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎች እንደሚያስፈልግ የአደጋ መከላከልና ዝግጅነት ኤጀንሲ እና የሰብዓዊ ዕርዳታ አጋር ድርጅቶች ነሐሴ 19 ቀን 1998 ዓ.ም በጋራ የዕርዳታ ጥያቄ አቅርበዋል::

ይኸው የዕርዳታ ጥያቄ በቀረበበት ወቅት በስብሰባው ላይ ለተገኙት የለጋሽ ሀገራት አምባሳደሮችና የረድኤት ድርጅቶች ተወካዮች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው ሌሎች እንግዶች ንግግር ያደረጉት የአደጋ መከላከልና ዝግጅነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን



መቻለ በዘንድሮው ክረምት በተለይም በሐምሌና ነሐሴ ወራት በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች የጣለው ከባድ ዝናብ በተለያዩ አካባቢዎች ባስከተላቸው ድንገተኛ ደራሽ እና የወንዝ ሙላት ጎርፍ አደጋዎች የሰው ሕይወት ጠፍቷል ፣ ንብረት ወድሟል ፣ እጅግ በርካታ የሆነ ሕዝብ ደግሞ በጎርፉ ሳቢያ ከቤት ንብረቱ ተፈናቅሎ ዕርዳታ ፈላጊ ሆኗል ብለዋል::

በድሬዳዋና ደቡብ ኦሞ ዞን የተከሰቱት የጎርፍ አደጋዎች ባስከተሉት ጉዳት 620 ሰው ሲሞት ከሐረርና ቤንሻንጉል ጉሙዝ በስተቀር ፣ በአማራ፣ ኦሮሚያ ፣ አፋር ፣ ሱማሌ፣ ጋምቤላ ፣ ትግራይ ክልሎች በተለያዩ ቦታዎች በተከሰቱ የጎርፍ አደጋዎች ሳቢያ 19 ሰው በጠቅላላው 639 ሰዎች በጎርፉ አደጋ ሕይወታቸውን አጥተዋል:: ከ30 ሺህ በላይ የቤት እንስሳት እና ግምቱ ለጊዜው ያልታወቀ ንብረት ተወስደዋል::

ምንም እንኳን በድሬዳዋ እና ደቡብ ኦሞ ዞን የተከሰቱት የጎርፍ አደጋዎች በሰው ሕይወት እና ንብረት ላይ ያስከተሉት ጉዳት ከፍተኛውን ድርሻ ቢይዝም በአማራ ፣ ኦሮሚያ ፣ አፋር ፣ ሱማሌ ፣ ጋምቤላ እና ትግራይ በደረሱት የጎርፍ አደጋዎች ሳቢያም በርካታ ሕዝብ ከቤት ንብረቱ ተፈናቅሎ ዕርዳታ ፈላጊ ሆኗል::

በድሬዳዋ በደረሰው ድንገት ደራሽ የጎርፍ አደጋ ሳቢያ 256 ሰው ሞቶ 10 ሺህ የሚሆን የከተማዋ ሕዝብ ለዓመታት ያፈራውን ጥሪት እንዲሁም የሚኖርበትን ቤት በጎርፍ ተነጥቆ የሌሎችን ዕርዳታ ፈላጊ ሆኗል:: በተመሳሳይ መልኩም በደቡብ ኦሞ ዞን በዳሰነች እና ኛንጋቶም



በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በተከሰተው የጎርፍ አደጋ ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉና ተጎጂ ለሆኑ 199 ሺህ ወገኖች መርጃ በጠቅላላው 27 ሚሊዮን 099 ሺህ 526 የአሜሪካን ዶላር ለአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ እና ለሌሎች ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎች እንደሚያስፈልግ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ እና የሰብዓዊ ዕርዳታ አጋር ድርጅቶች ነሐሴ 19 ቀን 1998 ዓ.ም በጋራ የዕርዳታ ጥያቄ አቅርበዋል::



ወረዳዎች የኦሞ ወንዝ ከመጠን በላይ በመሙላቱ በተከሰተው የውሀ መጥለቅለቅ 364 ሰዎች ሞተዋል ፣ እንዲሁም 3 ሺህ 200 የሚሆኑ የቤት እንስሳትና ከ1 ሺህ በላይ የእህል ጎተራዎች ተወስደዋል:: በዚሁ አደጋ ምክንያት በሁለቱ ወረዳዎች ነዋሪ የሆነ 10 ሺህ የሚሆን ህዝብ ከመኖሪያው ተፈናቅሏል::

በሌላም በኩል በአማራ ክልል በሪብ እና ጎመራ ወንዞች እንዲሁም የጣና ሀይቅ ሙላት በደቡብ ጎንደር በሊቦ ከምከም እና ፎገራ ወረዳዎች ፣ በምዕራብ ጎጃም በባህርዳር ዙሪያ እና ባህርዳር ከተማ በተጨማሪም በዳዋ ጨፋ እና አንጻኪያ ወረዳዎች በደረሱ ድንገተኛ ደራሽ የጎርፍ አደጋዎች ሳቢያ በጠቅላላው ከ13 ሺህ በላይ ሕዝብ ተፈናቅሎ በጊዜያዊ መጠለያ ይገኛል::

በኦሮሚያ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከ2 ሺህ በላይ ፣ በሱማሌ ሙስታሂል እና ቀላፎ ወረዳዎች ከ7 ሺህ በላይ ፣ በምዕራብ ትግራይ ቃፍታ ሁመራ ወረዳ ከ2 ሺህ በላይ ሠዎች በጎርፍ አደጋ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል::

በአጠቃላይ ለጎርፉ ተጋላጭ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከሚገኙት ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ዜጎች ውስጥ 200 ሺህ የሚጠጉ በጎርፍ አደጋ የተጎዱና ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸው ናቸው::

በዚሁ መሠረት ለነዚህ ወገኖች ከነሐሴ ወር ጀምሮ ለሚቀጥሉት ሦስት ወራት የሚቆይ ግምቱ 5 ሚሊዮን 184 ሺህ 675 የአሜሪካን ዶላር የሆነ 10 ሺህ 178 ሜትሪክ ቶን የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ያስፈልጋል::

ለሌሎች ምግብ ነክ ያልሆኑ የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፎች ደግሞ 13 ሚሊዮን 849 ሺህ 864 የአሜሪካ ዶላር የሚያስፈልግ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለጤና 5 ሚሊዮን 292 ሺህ 834 ፣ ለውሀ አቅርቦት 1 ሚሊዮን 307 ሺህ 170 ፣ለዘር 1 ሚሊዮን 177 ሺህ 854፣ ለጊዜያዊ መጠለያና ቁሳቁስ አቅርቦት 5 ሚሊዮን 081 ሺህ 256 ፣ ሕይወትን ለማዳን ሥራ 608 ሺህ 351 ፣ ለእንስሳት ጤና 382 ሺህ 399 የአሜሪካን ዶላር ያስፈልጋል::

በሌላ በኩልም በተለይም በድሬዳዋ እና ደቡብ ኦሞ ዞን በጎርፍ አደጋ ከቤት ንብረታቸወ የተፈናቀሉ ወገኖችን በቤት ግንባታ ፣ በመሠረተ ልማት ፣ ምግብ ነክ ባልሆኑ ቁሳቁሶች ፣ በኑሮ ገቢ ፣ በውሀ አቅርቦት ፣ በግብርና ፣ በጤና እና

በትምህርት ዘርፎች ለዘለቄታው መልሶ ለማቋቋም 8 ሚሊዮን3064 ሺህ 989 የአሜሪካን ዶላር ያስፈልጋል።

## ለጎርፍ አደጋ ተጎጂ ወገኖች ከ10 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ፣ ከ86 ሺህ በላይ የቁሳቁስ ፣ ከ14 ሺህ በላይ የአልባሳት እና 652 የመጠለያ ዕርዳታዎች ተከፋፍለዋል

በክረምቱ ወራት በተለይም በሐምሌና በነሐሴ ወራት በበርካታ የሀገራችን አካባቢዎች የጣለው ከባድ ዝናብ በተለያዩ አካባቢዎች ባስከተላቸው የጎርፍ አደጋዎች ሳቢያ ተጎጂ ለሆኑ 150 ሺህ በላይ ሠዎች እስከ ነሐሴ 25 ቀን 1998 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው 10 ሺህ 483.06 ኩንታል የምግብ እህል፣ አልሚ ምግብ ፣ ጥራጥ እና ዘይት ፣ በቁጥር 86 ሺህ 291 የተለያዩ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ፣ 15 ሺህ 131 ብርድ ልብስ ፣ 1 ሺህ 974 የቀን ልብሶች ፣ መጠናቸው 4x50 የሆነ 293 ጥቅል ኘላስቲክ ሽቶች ፣ በቁጥር 117 ኘላስቲክ ሽቶች ፣ 18 ሺህ 250 አጎበር እና 390 ድንኳኖች የሆኑ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ፍላጎቶች በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ሌሎች አካላት አማካይነት ተከፋፍለዋል።

የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ፍላጎቶቹ የቀረቡት በድሬዳዋ ፣ በደቡብ ሕዝቦች፣ አማራ፣ ኦሮሚያ ፣ አፋር እና ጋምቤላ ክልሎች በጎርፍ አደጋ ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ዕርዳታ ፈላጊ ለሆኑ ወገኖች መሆኑ ታውቋል።

ለጎርፍ አደጋ ተረጂዎቹ ከቀረቡት የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ፍላጎቶች ውስጥ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ የቀረበው በጠቅላላው 2051.06 ኩንታል የምግብ እህል ፣ አልሚ ምግብ ፣ ጥራጥ እና ዘይት ፣ 17 ሺህ 968 ልዩ ልዩ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ፣ መጠናቸው 4x50 የሆነ 61 ጥቅል ኘላስቲክ ሽቶች፣ 3 ሺህ 120 ብርድ ልብሶች፣ 1974 የቀን ልብሶች ፣ 18 ሺህ 250 አጎበሮች እና 5 ድንካኖች ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ በደቡብ ኦሞ ዞን በዳስነች እና ኛንጋቶም ወረዳዎች በጎርፉ ሳቢያ ጥሪታቸውን ለተቀሙ እና ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉት ወገኖች 737.7 ኩንታል የምግብ እህል ፣ አልሚ ምግብ ፣ ጥራጥሬ እና ዘይት ፣ 7 ሺህ 520 ልዩ ልዩ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ፣ መጠናቸው 4x50 የሆነ 30 ጥቅል ኘላስቲክ ሽቶች ፣ 1000 ብርድ ልብሶች እና 5 ድንኳኖች በአመዝኤ ፣ 1313.36 ኩንታል የምግብ እህል ፣ አልሚ ምግብ ፣ ጥራጥሬ እና ዘይት ፣ 10 ሺህ 488 የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ፣ 2120 ብርድልብሶች ፣ 31 ጥቅል ኘላስቲክ ሽቶች ፣ በቁጥር 117 ኘላስቲክ ሽቶች፣ 18250 አጎበሮች እና 1974 የቀን አልባሳት መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ፣



የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ፍላጎቶቹ የቀረቡት በድሬዳዋ ፣ በደቡብ ሕዝቦች፣ አማራ፣ ኦሮሚያ ፣ አፋር እና ጋምቤላ ክልሎች በጎርፍ አደጋ ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ዕርዳታ ፈላጊ ለሆኑ ወገኖች መሆኑ ታውቋል።

የግል ድርጅቶች ፣ ግለሰቦችና ሌሎች አካላት አማካይነት የተከፋፈለ ነው:: ቀሪው ደግሞ በከፋ እና ወላይታ ዞኖች በጎርፍ ለተጎዱ ወገኖች የተከፋፈለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::





በደቡብ ኦሞ ዞን በዳሰነች እና ኛንጋቶም ወረዳዎች በጎርፉ ሳቢያ ጥሪታቸውን ለተቀሙ እና ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉት ወገኖች 737.7 ኩንታል የምግብ እህል ፣ አልሚ ምግብ ፣ ጥራጥሬ እና ዘይት ፣ 7 ሺህ 520 ልዩ ልዩ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ፣ መጠናቸው 4x50 የሆነ 30 ጥቅል ኘላስቲክ ሸቶች ፣ 1000 ብርድ ልብሶች እና 5 ድንኳኖች በአመዝኤ ተካፋፍለዋል::

በተመሳሳይም በአመዝኤ አማካይነት ለጎርፍ አደጋ ተጎጂዎች ከቀረበው ጠቅላላ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ውስጥ 706 ኩንታል ምግብ፣ 27 ሺህ 310 ልዩ ልዩ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ፣ መጠናቸው 4x50 የሆነ 25 ጥቅል ኘላስተክ ሸቶች ፣ 4 ሺህ ብርድ ልብሶች ፣ 225 ድንኳኖች እንዲሁም 50 ካርቶን ሳሙና ለድሬዳዋ የጎርፍ ተጎጂ ወገኖች የቀረቡ ናቸው::

በአማራ ፣ በኦሮሚያ ፣ በአፋር እና ጋምቤላ ክልሎች በተለያዩ ቦታዎች በደረሰ የጎርፍ አደጋ ተጎጂ ለሆኑ ወገኖችም እንደ አደጋው ክብደትና የአደጋው ሠለባዎች ብዛት የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ አቅርቦት ተከናውኗል:: በዚሁ መሠረት ለአማራ 4562 ኩንታል ምግብ ፣ 25 ሺህ 70 ልዩ ልዩ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ፣ መጠናቸው 4x50 የሆነ 150 ጥቅል ኘላስቲክ ሸቶች እና 7 ሺህ 211 ብርድ ልብሶች ፣ ለኦሮሚያ 533 ኩንታል ምግብ፣ 15 ሺህ ልዩ ልዩ የቤት ለስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ፣ መጠናቸው 4x50 የሆነ 35 ጥቅል ኘላስቲክ ሸቶች፣ 130 ድንኳኖች እና 1 ሺህ 800 ብርድ ልብሶች ፣ ለአፋር 2 ሺህ 403 ኩንታል ምግብ እና መጠናቸው መጠናቸው 4x50 የሆነ 20 ጥቅል ኘላስቲክ ሸቶች እንዲሁም ለጋምቤላ 275 ኩንታል ምግብ እና መጠናቸው 4x50 የሆነ 2 ጥቅል ኘላስቲክ ሸቶች ተልከው ለተረጂዎች የተከፋፈሉ መሆኑ ታውቋል::

## በጐርፍ አደጋ ለተጐዱ ወገኖች መርጃ ከ ብር 23 ሚሊዮን በላይ ተለግሷል

በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች በተከሰቱ የጐርፍ አደጋዎች ሳቢያ ለዓመታት ያፈሩትን ቤት ንብረት አጥተው ለተፈናቀሉና ዕርዳታ ፈላጊ ለሆኑ ወገኖቻችን እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ 400 የሚሆኑ የመንግስትና የግል ድርጅቶች ፣ የሀይማኖት ተቋማት ፣ ልዩ ልዩ ማህበረሠቦች እና ግለሠቦች በጠቅላላው ብር 23 ሚሊዮን 282 ሺህ 890 የለገሡ መሆኑ ታወቋል::

ዕርዳታውን ከለገሡት ውስጥ አብዛኛዎቹ «የዚህ አይነቱ አፋጣኝ ምላሽ የሚሻ አደጋ በሚደርስበት ጊዜ ለወገን ደራሽ ወገን ነው» በሚል መርህ የተነሳሱ የሀገር ውስጥ የመንግስትና የግል ድርጅቶች ፣ የሀይማኖት ተቋማት ፣ ልዩ ልዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች እና ግለሠቦች ናቸው::

ከዚህ ዕርዳታ ውስጥ ብር 17 ሚሊዮን 321 ሺህ 023 በጥሬ ገንዘብ የተለገሠ ቀሪው ግምታቸው ብር 5 ሚሊዮን 961 ሺህ 867 በሆነ ልዩ ልዩ የምግብ ፣ የቤት ውስጥ

በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች በተከሰቱ የጐርፍ አደጋዎች ሳቢያ ለዓመታት ያፈሩትን ቤት ንብረት አጥተው ለተፈናቀሉና ዕርዳታ ፈለጊ ለሆኑ ወገኖቻችን እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ 400 የሚሆኑ የመንግስትና የግል ድርጅቶች ፣ የሀይማኖት ተቋማት ፣ ልዩ ልዩ ማህበረሠቦች እና ግለሠቦች በጠቅላላው ብር 23 ሚሊዮን 282 ሺህ 890 የለገሡ መሆኑ ታወቋል።

መገልገያ ቁሳቁሶች ፣ የመጠለያ እና የአልባሳት ዕርዳታ የተለገሠ መሆኑም ተመልክቷል።

ለጋሽ አካላቱ የገንዘብና የዓይነት ዕርዳታዎቹን ያበረከቱት በማዕከል በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ እና በድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር



ካውንስል ነው። በዚሁ መሠረት በጥሬ ገንዘብ ከተለገሠው ጠቅላላ ብር 17 ሚሊዮን 321 ሺህ 023 ውስጥ ብር 11 ሚሊዮን 521 ሺህ 023 በፌዴራል አመዝኤ ቀሪው ብር 5 ሚሊዮን 800 ሺህ በድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር ካውንስል የተለገሠ ነው። በተመሳሳይም በዓይነት ከተለገሠው ጠቅላላ ብር 5 ሚሊዮን 961 ሺህ 867 ውስጥ ብር 1 ሚሊዮን 361 ሺህ 867 በፌዴራል አመዝኤ ቀሪው ብር 4 ሚሊዮን 600 ሺህ ደግሞ በድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር ካውንስል የተለገሠ መሆኑ ታውቋል።

ይኸው ለወገን ተቆርቋሪ በሆኑ አካላት የተለገሠ ዕርዳታ ለዓመታት ያፈሩትን ሀብት ንብረት በጐርፍ አደጋ ተነጥቀው ባዶ እጃቸውን በመቅረት የሌሎችን ዕርዳታ ጠባቂ ለሆኑት ወገኖቻችን በአፋጣኝ እንዲደርስ የተለገሠ እንደመሆኑ መጠን ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለተጐዱት ወገኖች የሚያስፈልገው ዕርዳታ በፍጥነት እንዲደርሳቸው የሚደረግበትን ሁኔታ እንደሚያመቻች እና ዕርዳታውም ለታለመለት ዓላማ እንደሚውል በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ የዕርዳታ ርክክብ ሥነሥርዓቶች ላይ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ አረጋግጠዋል።

## በጐርፍ ለተጐዱ ወገኖች መርጃ ከ 1 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ በውጭ መንግስታትና ድርጅቶች ተለግሷል

በጐርፍ አደጋ ሳቢያ በልዩ ልዩ የሀገራችን ክፍሎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ዕርዳታ ለሚሹ ወገኖቻችን መርጃ የተለያዩ መንግስታትና የውጭ ድርጅቶች እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው 1 ሚሊዮን 083 ሺህ 740 የአሜሪካን ዶላር በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ በኩል የለገሡ መሆኑ ታውቋል።

ከዚሁ በተለያዩ መንግሥታትና የውጪ ድርጅቶች ከተለገሠ ዕርዳታ ውስጥ 80 ሺህ ዶላር በጥሬ ገንዘብ ቀሪው ደግሞ ግምታቸው 1 ሚሊዮን 3 ሺህ 740 በሆነ የምግብ ፣ የመጠለያ እና የመድሀኒት ቁሳቁሶች የተለገሠ እንደሆነም ለመረዳት ተችሏል።

በጥሬ ገንዘብ ከተለገሠው ዕርዳታ ውስጥ የቻይና ኖርዝ ኢንዱስትሪዎች ኮርፖሬሽን 50 ሺህ ዶላር ፣ የቻይና ቀይ መስቀል ማህበር 30 ሺህ ዶላር ለግሰዋል። በአይነት ከተለገሠው ዕርዳታ ደግሞ የሊቢያ መንግሥት ግምታቸው 617 ሺህ 565 ዶላር የሆነ የምግብና የመጠለያ ቁሳቁሶች ፣ የግብጽ

መንግስት ግምታቸው 316 ሺህ ዶላር የሆነ የምግብና የመድሃኒት ቁሳቁሶች ፣ የጃጠን መንግስት ግምታቸው44 ሺህ 674 ዶላር የሆነ የመጠለያና የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ቁሳቁሶች ፣ እንዲሁም የአልጄሪያ መንግስት ግምታቸው 25 ሺህ 501 ዶላር የሆነ የምግብና የመጠለያ ቁሳቁሶች ለግሠዋል።

መፈናቀል የየሀገሮቻቸው መንግስታትና ህዝቦች በእጅጉ ማዘናቸውንና ለተጐጂ ቤተሰቦች መፅናናትን መመኘታቸውን በተመሳሳይ ሁኔታ ገልፀዋል። ለጐርፍ አደጋ ተጐጂዎቹ በሚደረገው የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ፣ ቁሳቁስ ፣ መጠለያና መድሃኒት ዕርዳታ አቅርቦት እንዲሁም ተፈናቃዮቹን ለዘለቄታው ለማቋቋም ለሚደረግ እንስቅቃሴ

> በጐርፍ አደጋ ሳቢያ በልዩ ልዩ የሀገራችን ክፍሎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ዕርዳታ ለሚሹ ወገኖቻችን መርጃ የተለያዩ መንግስታትና የውጭ ድርጅቶች እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ባለው ገዜ ውስጥ በጠቅላላው 1 ሚሊዮን 083 ሺህ 740 የአሜሪካን ዶላር በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ በኩል የለገሡ መሆኑ ታውቋል።



ይኸንኑ በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ለጐርፍ ተጐጂ ወገኖቻችን መርጃ የተለገሠ ዕርዳታ በተለየዩ ጊዜያት ለአመዝኤ ያስረከቡት የለጋሽ መንግሥታቱና ድርጅቶች ተወካዮች ባደረጉት ንግግር በዘንድሮው ክረምት በሀገሪቱ የጣለው ከባድ ዝናብ ሳቢያ በተለያዩ ቦታዎች የተከሰቱት የጐርፍና የውሀ መጥለቅለቅ አደጋዎች ባስከተሉት የሕይወት መጥፋትና የንብረት ውድመት እንዲሁም በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጐች ከቤት ንብረታቸው የሚያደርጉት ድጋፍ ወደፊትም ቀጣይ እንደሚሆን ተናግረዋል።

ዕርዳታዎቹን የተረከቡት የአመዝኤ የሥራ ሀላፊዎችም በዚህ ዓይነት ፈታኝ ወቅት የሚደረግ ማንኛውም ፈጣን ዕርዳታ ጠ ቀሜታው ዕጅግ የጐላ መሆኑን በመግለጽ ለተደረገው ዕርዳታ በተረጂ ወገኖች ፣ በኤጀንሲውና በኢትዮጵያ መንግሰት ስም ለለጋሽ መንግስታቱ እና ድርጅቶቹ ምስጋና አቅርበዋል።